እኔ በሰማይ ላለው (ለአላህ) ታማኝ ሆኜ፤ የሰማይ ወሬም ጠዋትና ማታ እየመጣልኝ አታምኑኝምን?!።

ከአቡ ሰዒድ አልኹድሪይ (ረዺየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «ዐሊይ ቢን አቢ ጧሊብ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ከየመን በቀረዝ ቅጠል ታሽቶ በተዘጋጀ ከረጢት ከማዕድኑ አፈር ያልጠራን የወርቅ ቁርጥራጭ ወደ አላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ላከ። እሳቸውም ለአራት ሰዎች አከፋፈሉት። እነርሱም ዑየይና ቢን በድር፣ አቅረዕ ቢን ሓቢስ፣ ዘይድ አልኸይሊና አራተኛው ወይ ዐልቀማ ነው ወይም ዓሚር ቢን ጡፈይል ነው። ከርሳቸው ባልደረባ መካከል የሆነ አንድ ሰውዬም: "ከነዚህ የበለጠ እኛ የተገባን ነበርን!" አለ። ይህ ወሬም ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ዘንድ ደረሰና እንዲህ አሉ: "እኔ በሰማይ ላለው (ለአላህ) ታማኝ ሆኜ፤ የሰማይ ወሬም ጠዋትና ማታ እየመጣልኝ አታምኑኝምን?!።" በዚህ ጊዜም አንድ አይኑ የጎደጎደ፤ ከአይኑ ስር ያሉት አጥንቶቹ ወጣ ያሉ፤ ከቅንድቡ በላይ ያለው ግንባሩም ወጣ ያለ፤ ፂሙ የበዛ፤ ጭንቅላቱ የተላጨ፤ ሽርጡን ከቁርጭምጭሚቱ በላይ ከፍ አድርጎ የታጠቀ ሰውዬ ቆመና: "የአላህ መልክተኛ ሆይ! አላህን ይፍሩ!" አላቸው። እርሳቸውም "ወዮልህ! ከምድር ነዋሪዎች ባጠቃላይ አላህን ለመፍራት የተገባሁ እኔ አይደለሁምን?" አሉ። ከዚያም ሰውዮው ዘወር አለ። ኻሊድ ቢን ወሊድም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! አንገቱን ልቅላውን?" አላቸው። እርሳቸውም "በፍፁም! ምናልባት እርሱ ይሰግድ ይሆናል።" አሉ። ኻሊድም "ቀልቡ ውስጥ የሌለውን እምነት (ለይዩልኝ) በአፉ እየተናገረ የሚሰግድ ስንት ሰው አለ አይደል እንዴ?!" አላቸው። የአላህ መልክተኛም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) "እኔ የሰዎችን ቀልብ እንድሰነጥቅ፤ ሆዳቸውንም ከፍቼ እንድመለከት አልታዘዝኩኝም።" አሉ። ከዚያም
ወደዚህ ሰውዬ ጀርባውን ሰጥቶ እየተመለከቱት እንዲህ አሉ: "ከዚህ ሰውዬ ዘርና ባልደረቦች የሆኑ የአላህን መጽሐፍ ቀሏቸው
የሚያነቡ፤ የሚቀሩት ግን ከጉሮሮዋቸው የማያልፍ፤ ቀስት ሲወረወር ከኢላማው እንደሚሾልከው ከእስልምና ሾልከው የሚወጡ ሰዎች
ይመጣሉ።" እንዲህም ብለዋል ይመስለኛል: "እኔ ከደረስኩባቸው የሠሙድ ህዝቦችን አገዳደል እገድላቸዋለሁ።"»
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ዐሊይ ቢን አቢ ጧሊብ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - በቀረድ ታሽቶ በተሰራ ከረጢት ከአፈሩ ያልፀዳ የወርቅ ቁርጥራጮችን ከየመን ወደ አላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ላከ። ነቢዩም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ለአራት ሰዎች አከፋፈሉት። እነርሱም: ዑየይና ቢን በድር አልፈዛሪይ፣ አቅረዕ ቢን ሓቢስ አልሐንዞሊይ፣ ዘይድ አልኸይሊ አንነብሃሊይ፣ ዐልቀማ ቢን ዐላሠህ አልዓሚሪይ ናቸው። ከርሳቸው ባልደረባ የሆነ አንድ ሰውዬም እንዲህ አለ: "በዚህ ስጦታ ከነዚህ በበለጠ እኛ የተገባን ነን።" ይህም ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ዘንድ ደረሰና እንዲህ አሉ: "እኔ በሰማይ ላለው (አላህ) ታማኝ ሆኜ የሰማይ ወሬ ጠዋትና ማታ እየመጣልኝ አታምኑኝምን?!" አይኖቹ ገባ ገባ ያሉ፤ የጉንጩ የላይኛው አጥንት ወጣ ያሉ፤ ግንባሩም ወጣ ያለ፤ ፂሙ ሳይረዝም የበዛ የሆነ፤ ጭንቅላቱን የተላጨ፤ የታችኛውን የሰውነት አካሉን የሚሸፍነው ሽርጡ ከፍ ያለ አንድ ሰውዬ ቆመና: "የአላህ መልክተኛ ሆይ! አላህን ይፍሩ!" አላቸው። እርሳቸውም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) "ወዮልህ! ከምድር ነዋሪዎች ባጠቃላይ አላህን ለመፍራት የተገባሁ እኔ አይደለሁምን?" አሉት። ከዚያም ሰውዬው ዞሮ ሄደ። ኻሊድ ቢን ወሊድም: "የአላህ መልክተኛ ሆይ! አንገቱን አልቅላውምን?" አላቸው። እርሳቸውም "በፍፁም! ምናልባት የሚሰግድ ሊሆን ይችላል።" አሉት። ኻሊድም: "በቀልቡ የሌለውን በአፉ የሚናገር ስንት ሰጋጅ አለ?" አለ። እርሳቸውም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን): "እኔ የሰዎችን ቀልብ እንድሰነጥቅም ሆነ ሆዳቸውን ቀድጄ እንድመለከት አልታዘዝኩም። እኔ የታዘዝኩት ሰዎችን በውጫዊ ማንነታቸው እንድይዛቸው ነው።" አሉ። ከዚያም ሰውዬው ጀርባውን ሰጥቶ መሄዱን ሳለ እየተመለከቱት እንዲህ አሉ: "ከዚህ ሰውዬ ዘር፣ ከባልደረቦቹ ወይም ከጎሳዎቹ መካከል የአላህን መጽሐፍ በጥሩ ድምፅ አሳምረው በመቅራት ምርጥ ችሎታው ያላቸው፤ አብዝተው ከመቅራታቸውም ምላሳቸው ርጥብ የሆኑ፤ ንባባቸው ግን ከጉሮሮዋቸው የማታልፍ። ከጉሮሮ አልፋ ቀልባቸው ጋር ደርሳ የምታስተካክላቸው ያልሆነች፤ ንባባቸውን አላህ ከፍ የማያደርጋትም የማይቀበላትም፤ ቀስት ከኢላማው በላይ ፈጥኖና በቀላሉ እንደሚወጣው ከእስልምና የሚወጡ ህዝቦች ይመጣሉ።" እንዲህም ብለዋል ይመስለኛል: "በሰይፋቸው በሙስሊሞች ላይ መውጣታቸውን ብደርስበት ኖሮ እንደ ሠሙድ ህዝቦች አገዳደል ከባድ አገዳደልን እገድላቸው ነበር።"

